# ትዝብት

ከወንድሙ መኰንን

## ቁጭ-በሉ በቤይጂንግ ብቅ አሉ?

የኢትዮጵያ ሚሌኒየም ዓመት ሊሞላው ጥቂት ሳምንታት ቢቀሩትም የቅርብ ትዝታ ፈጥሮ አልፏል። ስንት ጉድ ታየ! ስንት ጉድ ተሰማ! ስንት ትዝብት ጣለ! ለማንኛው ሳይደገምብን ቶሎ ነቀተን የሚሌኒየሙን አፈዝ አደንዝዝ ዝግጅት መተት እንደምንም አልፈነው ዛሬ ደርሰናል። በታወቁት የጭፈራ አዘጋጆች፣ ዓለም-አቀፍ ቁጭ-በሉዎች (con artists) ተከሸና የቀረበችውን ዳንኪራ፣ የኢትዮጵያው ጠቅላይ ስቃይ (Prime Misery) በሱዳንኛ ዘፈን ከውዷ ባሌበታቸው "(ቀዳማይ እመቤት" (ድንቄም!) - እንዲያው በሞቴ ቃሉን ከየት አመጡት?) ሲምነሸነሹባት ዓይተን እንዳላየን አልፈናል። ጊዜ፣ ውይይት ታክሲ አይደለም፤ ቁሞ አይጠብቅም ይባላል። ሁሉም አለፈ። ከሎንዶንና ከካናዳ ኢምፖርት የተደረጉት ቁጭ-በሎዎችም ሆኑ ጌቶቻቸው ያሰቡት አልተሳካላቸውም። የተጠበቀው የመስቀል አደባባይ ትዕይንትም አልተደረገም። እኛም ከዚህ በኋላ እነዚህን ጉደኞች ከማየት የተገላገልን መስሎን ነበር። እነሱ እዚያ የተበከለ ዘገጅት አዘጋጅተው ስደተኛውን ሕብረተሰባችንን እንዳያጠምዱት በማሰብ  ጊዘያዊ ኮሚቴ ተቋቁሞ በአስቸኳይ  አማራጭ  ፈጥሮ፤ ሎንዶን ነዋሪ የሁኑት ኢትዮጵያውን አገር ውስጥ ያሉት ዜጎቻችን ያለገኙትን ዕድል አግኝተው ትራፋልጋር አደባባይ ላይ ከ10 እስከ 15 ሺህ ሕዝብ አሰባስበው እንግሊዝን "ጉድ!" (WOW!) አሰኝተው ሚሌኒያማችንን አክብረዋል። ኢትዮጵያ ውስጥ የቁጭ-በሉዎቹና የጌቶቻቸው መፈንጠዣ ዝግጅት ሆኖ ሌላው የበይ ተመልካች ሆኖ ሲቀር፤ የሎንዶኑ ዝግጅቱ እስከ ዛሬ ድረስ የከተማው ትዝታ ሆኖ በሎንዶን ሕዝብና ከንቲባዎች ሕሊና ውስጥ ተቀርጾ ይታወሳል።

ወያነኔና ዓለም-ዓቀፉ ቁጭ-በሉዎች የሚሌኒየሙን ዝግጅት አገር ቤት እንደዚያ ካንበጫረቁት ወዲህ፤ በታላቅ ጉጉት ይጠበቅ የነበረው ሌላው ዝግጅት የቤይጂንጉ ኦሎምፒክ ነበር። አባዛኛው ሰው የጓጓው የወያኔን ካድሬዎች፣ ያቺኑ ያጎሳቆሏትን ሰንደቅ ዓላማ ተሸክመው ሲያልፉ ማየት ሳይሆን ብረቅዬ የኢትዮጵያ አትሌቶችን በመግቢያው ዕለት ኢትዮጵያዊነት ፀዳልን ተላብሰው ሲያልፉ ማየት ነበር። የቤይጂንግ አየር የተበከለ ስለሆነ የኛ አትሌቶች ዘግየት ብለው እንደሚሄዱ ስለተሰማ፤ ኢትዮጵያዊው ወገን የጓጓላቸውን ስፖርተኞች የማየት ዕድል እንደማይኖረው ከወዲሁ አውቆት የመክፈቻ ትርዒቱን ሳይመለከተው በመቅረቱ፣ ብዙ ነገር አምልጦት ነበር።



ካመለጡት ዕድሎች መሐል የታዋቂው ኢትዮጵያዊ አትሌት፣ የምሩጽ ይፍጠር በወያኔ አርማ የተተበተበችውን ሰንደቅ ዓላማ ተሸክሞ ብቅ ማለቱ ነው። ምሩጽ ይፍጠር በተአምር ከስደት ተመልሶ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ እያውለበለበ አለፈ ሲባል፣ "ተንቀሳቃሽ ስዕሉን የቀረጻችሁ" እየተባለ እንደገና ካለፈ በኋላ እየተዋከበ ለማየት ተገዷል። ከተዋከቡት ዜጎቻችን መሀል፤ ይኽ ጸሐፊ አንዱ ነበር። ዕውነትም ምሩጽ ነበር ጎስቋላ ሰንደቅ ዓላማዩቱን የተሸከመው። ምሩጽ በሩጫ ካገር ወጥቶ በሩጫ ተመለሰ እንበል?

የሰንደቅ ዓላማ ነገር ከተነሳ አይቀር አንድ ነገር እንበል። ወያኔ ጨርቅ ብሎ የጠራውን ሰንደቅ ዓላማችንን ጨርቅነቱን ለማረጋገጥ ብሎ ይመስላል ጭራሹኑ በክሎታል። ከመሀሉ ጉብ ያለውን የአሽታሮት ምልክት ማየት አያበግንም፣ ጎበዝ? ሰንደቅ ዓላማችን ላይ የማይሽር ቁስል የሚመስለውን የጥንቆላ ኮከብ እራፊ ለጣጥፈውበት ማየት ቆሽት ያደብናል። መተት አስጠንቁለው መሆን አለበት። አሁን ምን አለ ያንን እንኳን ቢተውት!

ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ተንቀሳቃሽ ስዕል በማስሊያ መኪናዎ ቀስት ጠቁመው እስቲ ላንድ አፍታ ልብ ብለው የበይጂንጉን ኦሎምፒክ አከፋፈት ሥነ ሥራዐት ያስተውሉት። ምን ይታይዎታል? ከምሩጽ ባሻገር የሚያዉቁት ገጽ አለ?

http://blip.tv/file/1157437

እስቲ እንድገና ትኩር ብለው አዩት? አስተዋሉት? እንርዳዎት! አዎ ምሩጽ አሁን ይሩጥ ወይ አይሩጥ ባይታወቅም፤ ሰንደቅ ዓላማዋን እያውለበለበ በፈገግታ ፊት ፊት ሰከም ሰከም እያለ አልፏል። መኖር ደግ ነው። የሞተ ብቻ ነው የተጎዳው። ማሞ ወልዴም በእሥር ማቅቆ ሕይወቱ ባታልፍ ኖሮ፣ እሱም እንደዚሁ በክብር በታላላቅ የየሀግራቱ መሪዎችና እንግዶች ፊት ባለፈ ነበር። ቀጥላ አንድ የኢትዮጵያን ገጽና ልብስ የተላበሰች ፍልቅልቅ ኢትዮጵያዊት ደርባባ ሴት ትታያለች። አምሮባታል። በምንም ዓይነት የስፖርተኛ ቅርጽ ግን አያትይባትም! ከየት የመ|ጣች ናሙና ናት? ስለ ስፖርተኝነቷ የታወቀ ነገር ባይኖርም፣ እስፖርተኞቻችንን ወክላ አልፋለች። እሷስ ትሁን! ከምሩጽ በስተቀር፤ እንድያውም ስፖርተኛ እዚያ ውስጥ ሽታው ያለም አይስመስልም።

ከዚያ በኋላ ያለፉት ማንነታቸው በቅጡ ያልታወቁ የእስፖርተኛው ሕብረተሰብ ወኪሎች ነን ባዮች መሀል አንድ ጉድ ፈላ። ዓይናችሁን ለሰኮንድ ከጨፈናችሁ ሊያመልጣችሁ የሚችል  ጉደኛ ገጸ ባሕርይ ውልብ ብሎ ሲያልፍ ይታያል። ስዩም በረደድ ናቸው ወይስ ጣዕረ ሞታቸው (ghost)? ይኸ ጸሐፊ፤ ዓይኑ ሸፍጥ (ትሪክ) የሠራበት መስሎት ጭፍን ጭፍን እያደረገ ሲያጮልግ የማየት ችሎታውን ተጠራጥሮት ነበር። “ዓይኔ ነው - ባሌ ነው” ያለችው ብጤ መሆኑ ነው። መልሶ መላልሶ (after repeatedly rewinding) ቢያየው ችግሩ ከዓይኑ ሳይሆን ተንቀሳቃሽ ሥዕሉ ላይ የሚታየው ገጸ ባሕርይ በትክክል የሚሌኒየሙ ድግስ አቀባባሪ ቀንደኛው የሎንዶኑ ቁጭ-በሉዎች መሀል፤ ቆንጮው ሰውዬ ሆነው አግኝቶአቸዋል። ይኸቺ ናት ጨዋታ! እንዴት ተደርጎ! ሰሞኑን በፎርቹን ጋዜጣ፤ “እንዴት ሊታወሱ የፈልጋሉ (How do you want to be remembered) ሲባሉ፤ ”ዛፍ አፍቃሪ” (Tree Lover) ነኝ” ባዩ የሎንዶኑ ቁጭ-በሉ በየት በየት አርገው ነው በቤይጂንግ ብቅ ያሉት! አይ የኢትዮጵያ አየር መንገድ! የማትሸከመው፣ የማት ጭነው ጉድ የለ! የሚሌኒየሟ የምትታለብ ላም ነጠፈች መሰል፤ ቀጣይዋ የካሽ ጥገት ፕሮጀክታቸው ይኸች ነበረች ማለት ነዋ! እሳቸውን በግል የሚያውቁት ሲነገሩን፤ ከሁለትና ከሶስት ዓመት አስቀድመው የመተንበይ ችሎታቸውን ያደንቁላቸዋል። እንዲያ ከሆነማ እግዚኦ! አድነነ ከመዓቱ ይሰውረነ እንጂ ምን ይባላል።

ለማንኛውም፣ ስፖርተኞቻችን ጸሎት ያሻቸዋል።፡አትሌቶቻችንን መልካም ዕድል በቤይጂንግ ኦሎምፒክ እንዲገጥማቸው እንመኝላቸው። መዳሊያዎቻቸውንና ሽልማቶቻቸውንም ቁጥጥራቸው ሥር ካዋሉአቸው ቁጭ-በሉዎች አምላክ እንዲጠብቅላቸውም ለጸሎት ተነሱ!